በቻይና ህዝባዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገ በፍትሀብሔር እና የንግድ ህግ ጉዳዮች የጋራ ፍትህ ትብብር ስምምነት

የቻይና ህዝባዊት ሪፐብሊክ መንግስት እና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት (ከዚህ በኋላ በጋራ "ወገኖች" በተናጠል "ወገን") እየተባሉ የሚጠሩ ይሆናል፡፡

በሁለቱም ሀገራት መሀከል የሚኖረውን የፍትሀብሔር እና የንግድ ህግ ጉዳዮችን የጋራ ትብብር እና ጥቅምን እኩልነትን መሰረት በማድረግ ለማጠናከር፤

ያለውን የወዳጅነት ግንኙነት የበለጠ ለማሳደግ እና ለማጠናከር በማሰብ፤

ከዚህ እንደሚከተለው ተስማምተዋል፡፡

ምዕራፍ አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች
አንቀፅ 1
የህግ ትብብር ወሰኑ

1. ሁለቱም ወገኖች የሀገራቸውን ህግ መሰረት በማድረግ ሰፊ በሆነ ሁኔታ በዚሁ ስምምነት በተሸፈነው አግባብ የጋራ የሆነ ህጋዊ ትብብር ለማድረግ ተስማምተዋል፡፡

2. በዚህ ስምምነት የህግ ትብብር የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

ሀ. የፍ/ቤት ሰነዶችን የሚመለከቱ ጉዳዮችን፤
ለ. ማስረጃዎችን የመውሰድ፤
ሐ. የግልግል ዳኝነት እና የፍ/ቤት ውሳኔዎችን እውቅና የመስጠት እና የመፈጸም፤
መ. ህግን በተመለከተ መረጃ መለዋወጥን የሚመለከቱ ተግባራትን ያጠቃልላል፡፡

አንቀፅ 2
የህግ ክለላ

1. አንደኛው ወገን በራሱ ግዛት ውስጥ የሌላኛውን ወገን ዜጋ እንደራሱ ሀገር ዜጋ በተመሳሳይ ሁኔታ የህግ ከለላ የመስጠትና በፍርድ ቤት የመዳኘት መብቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. የአንደኛው ወገን ፍ/ቤት የሌላውን ወገን ዜጋ ቋሚ የሆነ መኖሪያ ወይም መቀያ የለህም እንዲሁም ደግሞ የውጭ ሀገር ዜጋ ነህ በሚል ምክንያት ብቻ ለሚደረግ ክርክር ወጪ የሚሆን ዋስትና እንዲያቀርብ አያስገድደውም፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች በተዋዋይ ሀገራት ህጎች መሰረት በአንዱ ወገን ግዛት ክልል ውስጥ ተቋቁመው በሚገኙ ህጋዊ ሰውነት በተሰጣቸው ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

አንቀፅ 3
የህግ ትብብር እና ክርክር ክፍያን ስለመቀነስ እና ነፃ ስለመሆን

1. የአንዱ ወገን ዜጋ በሌላኛው ወገን ግዛት ውስጥ በተመሳሳይ ሁኔታ እንደ ራሱ ወገን ዜጋ ክስ ሂደት ክፍያ ቅነሳ ወይም ነፃ አገልግሎት እንዲሁም የህግ እርዳታ አገልግሎት ተጠቃሚ ይሆናል።
2. በንኡስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰውን መብት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታ አመልካቹ በሚኖርበት ቋሚ መኖሪያ ወይም መቀያ ክልል ውስጥ አግባብ ባለው ባለስልጣን በሚሰጥ የግለሰቡን የፋይናንስ ሁኔታ የሚያሳይ ሰርተፊኬት ጋር ተደግፎ መቅረብ አለበት። አመልካቹ በተዋዋይ ወገኖች ግዛት ክልል ውስጥ ቋሚ የሆነ መቀያ ወይም መኖሪያ ከሌለው ሀገሩን በሚወክለው የዲፕሎማሲ ወይም የቆንስላ ወኪል በኩል ሰርተፊኬቱ ሊወጣ ወይም ሊፀድቅ ይችላል።
3. የህግ ባለስልጣናት ወይም ሌላ አግባብ ያለው ባለስልጣን ተጨማሪ መረጃዎችን የመጠየቅና ለአመልካቹ የህግ ትብብር ወይም የክስ ሂደት ክፍያ ቅነሳ ወይም ነፃ ስለመሆን የመወሰን ኃላፊነት አለበት።

አንቀፅ 4
የህግ ትብብር ማድረጊያ መንገዶች

1. በዚህ ስምምነት በተለየ ሁኔታ ካልተቀመጠ በስተቀር ሁለቱም ወገኖች የህግ ትብብር ለመጠየቅም ወይም ለመስጠት ጥያቄ የሚያቀርቡት በቀጥታ በወከሏቸው ዋና ባለስልጣናት በኩል ይሆናል።
2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፁት ዋና ባለስልጣናት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ፍትህ ሚኒስቴር እና የህዝባዊት ቻይና ሪፐብሊክ መንግስት ፍትህ ሚኒስቴር ይሆናሉ።
3. አንዱ ወገን የወከለውን ዋና ባለስልጣን ሲቀይር ለሌላኛው ወገን የተቀየረውን ባለስልጣን በዲፕሎማሲያዊ የግንኙነት መንገድ መሰረት ማሳወቅ ይኖርበታል።

አንቀፅ 5
ለህግ ትብብሩ ተፈፃሚ ስለሚሆኑ ህጎች

በዚህ ስምምነት በተለየ ሁኔታ ካልተቀመጠ በስተቀር ሁለቱም ወገኖች የህግ ትብብር ለማድረግ የሀገራቸውን ህጎች ተፈፃሚ ያደርጋሉ።

አንቀፅ 6
የህግ ትብብር ስምምነትን ስለአለመቀበል

1. የተጠየቀው ወገን በህግ የመተባበር ጥያቄው የራሱን ሀገር ሉአላዊነት፣ ደህንነት፣ መሰረታዊ የህዝብ ጥቅምን ወይም ከሀገሪቱ ህጎችና መሰረታዊ መርሆዎች ጋር የሚፃረር ወይም ጥያቄው ከህጋዊው ባለስልጣን በላይ ሲሆን ያለመቀበል እና ያልተቀበለበትንም ምክንያት ለጠየቀው ወገን ማሳወቅ አለበት።
2. የህግ ሰነዶችን ወይም ማስረጃዎችን እንዲሰጥ የሚቀርብ ጥያቄ በጉዳዩ ላይ ስልጣን ያለው የእኔ ፍ/ቤት ብቻ ነው ወይም ደግሞ የሀገሪቱ ህግ ይህን ለማድረግ አይፈቅድም በሚል ምክንያት ብቻ ሌላኛው ወገን ሊከለከል አይገባም።

አንቀፅ 7
በህግ ጉዳዮች የመተባበር ስምምነት ይዘትና ቅርጽ

1. በህግ ጉዳዮች የመተባበር ስምምነት ጥያቄ የሚቀርበው በጽሁፍ ሆኖ ፊርማ ወይም የጠያቂው ባለስልጣንን ማህተምና ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን :-
   ሀ. የጠያቂውን ባለስልጣን ስምና አድራሻ፣
   ለ. የሚቻል ከሆነ የተጠያቂዉን ባለስልጣን ስም፣
   ሐ. ጉዳዩ የሚመለከተውን ሰው ስም፣ ዜግነት እና አድራሻ፣ ህጋዊ ሰውነት ያለው ከሆነ ስሙንና አድራሻውን፣
   መ. አስፈላጊ ሲሆን የሚመለከተው ወገንን ተወካይ ስምና አድራሻ፣
   ሠ. ከጥያቄው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መግለጫዎች እና ስለ ጉዳዩ አጭር ማጠቃለያ፣
   ረ. የሚፈለገውን ትብብር መግለጫ እና
   ሰ. ጥያቄውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን ይይዛል።
2. ተጠያቂው ወገን በዚህ ስምምነት መሰረት ጥያቄውን ለመመለስ በጠያቂው ወገን የቀረበው መረጃ በቂ አይደለም ብሎ ሲያምን ጠያቂውን ወገን ተጨማሪ መረጃ መጠየቅ ይችላል።

አንቀፅ 8
ቋንቋ

1. የሁለቱም ወገን ባለስልጣናት በጽሁፍ ለሚያደርጉት ግንኙነት የራሳቸውን ብሔራዊ ቋንቋ ከእንግሊዘኛ ቋንቋ ትርጉም ጋር በማስደገፍ ይጠቀማሉ፡፡
2. በዚህ ስምምነት በተለየ ሁኔታ ካልተቀመጠ በስተቀር በህግ ጉዳዮች ላይ የሚቀርብ የትብብር ጥያቄና አጋዥ ሰነዶችን በተመለከተ የጠያቂው ወገን ቋንቋን ከሌላኛው ወገን ቋንቋ ትርጉም ወይም ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ትርጉም ጋር በማስደገፍ ይቀርባል፡፡

ምዕራፍ ሁለት
የህግ ሰነዶች አገልግሎት
አንቀፅ 9
የተፈፃሚነት ወሰን

በዚህ ስምምነት በተገለፀው መሰረት የሚቀርብ የህግ ሰነዶች ግልጋሎት ጥያቄ በሌላኛው ወገን ግዛት ውስጥ በሚገኙ ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ያደርጋል፡፡

አንቀፅ 10
የህግ ሰነዶች ግልጋሎት አፈፃፀም

1. የተጠየቀው ወገን የቀረበውን ጥያቄ በህጉ በተገለፀው መሰረት በወቅቱና የራሱን ህግ በማይፃረር መንገድ በተለይ ደግሞ ጠያቂው ወገን በጠየቀው መሰረት ውጤታማ አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡
2. የተጠየቀው ወገን ጥያቄውን ለመፈፀም የማይችል ከሆነ መፈፀም ለሚችለው አግባብ ላለው ባለስልጣን ማስተላለፍ አለበት፡፡
3. የተጠየቀው ባለስልጣን ጠያቂው በገለፀው አድራሻ መሰረት አገልግሎቱን ለመስጠት አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ የተጠየቀው ወገን የተሰጠውን አድራሻ የማረጋገጥና አስፈላጊ ከሆነም ጠያቂውን ወገን ተጨማሪ መረጃ በመጠየቅ አስፈላጊ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፡፡ ተጠያቂው ወገን አሁንም አድራሻውን እርግጠኛ ባለመሆን ወይም በሌላ ምክንያት ጥያቄውን መፈፀም ካልቻለ መጠየቂያውን ከአጋዥ መረጃዎቹ እና ለአገልግሎቱ አለመፈፀም ምክንያት የሆነውን ነገር በመግለፅ ለጠያቂው ወገን መመለስ አለበት፡፡

አንቀፅ 11
ውጤትን ስለማሳወቅ

1. ተጠያቂው ወገን በዋና ባለስልጣኑ በኩል ውጤቱን ለተጠያቂው ወገን በፅሑፍ ግልጋሎቱን በፈፀመው ባለስልጣን በተረጋገጠ ማስረጃ ያስታውቃል።
2. ማስረጃው መረጃ የተጠየቀበትን ሰው ስም፣ ማንነት ፣ ቁን ፣ቦታ እና የተሰጠውን የአገልግሎት አይነት መያዝ አለበት። የተጠቀሰው ሰው ጥያቄውን ለመቀበል ፈቃደኛ ካልሆነ ላለመቀበሉ ምክንያት የሆነውን ነገር መግለፅ አለበት።

አንቀፅ 12
የአገልግሎት ዋጋ

ተጠያቂው ወገን በራሱ ግዛት ውስጥ ለተጠየቀው ጉዳይ ማስፈፀሚያ የአገልግሎት ዋጋ ራሱ ይከፍላል። ነገር ግን ጠያቂው ወገን በአንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በተለየ መንገድ ለሚፈጸም ጥያቄ የአገልግሎት ክፍያ እሱ ይከፍላል።

ምዕራፍ ሦስት
ማስረጃዎችን ስለመውሰድ
አንቀጽ 13
የተፈፃሚነት ወሰን

1. ማስረጃ መውሰድን በተመለከተ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ለጉዳዩ ባለቤት የሆኑትን ወገኖች እና የምስክሮችን ቃል፣ የሰነድ እና ግዑዛዊ ማስረጃዎችን፣ የባለሙያ ግምገማ ማድረግን፣ የፍ/ቤት ማጣሪያዎችን እና ሌሎች የህግ ተግባራትን መፈፀም ጨምሮ በዚህ ስምምነት መስራት ሌላኛው ወገን መፈፀም አለበት
2. ይህ ስምምነት ከዚህ በታች ለተገለጹት፡-
   ሀ. ህጋዊ ክርክር ለማድረግ ለማይገመትበት ፣ ላልታቀደበት እና በማይነሳበት ጉዳዮች፤
   ለ. በጥያቄው ላይ ባልተጠቀሱ ፣ ቀጥተኛ እና የቅርብ ግንኙነት በሌላቸው ጉዳዮች ላይ ማስረጃ መቀበልን አያካትትም ።

አንቀፅ 14
ማስረጃዎች ስለሚወሰድበት አፈፃፀም

1. የተጠየቀው ወገን በሀገሩ ህግ መሰረት ጥያቄዎችን በወቅቱ ማስተናገድ አለበት፡፡
2. ተጠያቂው ወገን የሚቀርብለት ጥያቄ የሀገሪቱን ህግ እስካልተቃረነ ድረስ ሌላኛው ወገን በተለየ ሁኔታ በግልጽ በጠየቀው መንገድ የማስረጃ መውሰድ ጥያቄውን ተቀብሎ መፈፀም አለበት፡፡
3. የተጠየቀው ባለስልጣን ጥያቄውን ለመመለስ የማይችል ከሆነ ጥያቄውን ለሚመለከተው ባለስልጣን እንዲፈፅም ያስተላልፋል፡፡
4. የተጠየቀው ወገን ጠያቂው ወገን በጠቀሰው አድራሻ መሰረት ለማግኘት አስቸጋሪ ሲሆን አድራሻውን ለማረጋገጥና አስፈላጊ ሲሆን ተጨማሪ መረጃ ከጠያቂው ወገን መጠየቅ ይችላል፡፡ አሁንም ወገን በአድራሻው ወይም በሌላ ምክንያት ጥያቄውን መመለስ ካልቻለ መጠየቂያውን፣ አጋዥ የመረጃ ሰነዶችንና ለመፈፀም ያልቻለበትን ምክንያት በመግለጽ ለጠያቂው ወገን መመለስ አለበት፡፡
5. ጠያቂው ወገን በግልጽና በተሟላ ሁኔታ ሲጠየቅ የሚመለከታቸው ወገኖች ወይም ተወካዮቻቸው እንዲቀርቡ ለማድረግ ጥያቄው መቼ እና የት እንደሚፈጸም ማሳወቅ አለበት፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ባለጉዳዮች ወይም ወኪሎቻቸው በሚቀርቡበት ወቅት የሀገሪቱን ህግ ተከትሎ ተፈፃሚ የሚደረግ ይሆናል፡፡

አንቀፅ 15
ማስረጃዎችን ለመስጠት አለመቻል

1. በዚህ ስምምነት መሰረት ማስረጃ እንዲሰጥ የሚፈለገው ሰው በጠያቂው ወገን ህግ መሰረት ማስረጃውን ያለመስጠት መብት አለኝ ብሎ ሲቃወም የተጠቀሰውን ልዩ መብት መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ አንዲቀርብለት ተጠያቂው ወገን ሌላኛውን ወገን ይጠይቃል፡፡ በግልጽ ሌላ ተግራሪ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ በጠያቂው ወገን ልዩ መብት መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ መቅረብ እንደመጨረሻ ወይም አስተማማኝ ማስረጃ ይቆጠራል፡፡
2. በዚህ ስምምነት መሰረት ማስረጃ እንዲሰጥ የሚጠየቀው ግለሰብ በተጠያቂው አገር ውስጥ በሚነሳ ተመሳሳይነት ባለው ክርክር ላይ ማስረጃ እንዳይሰጥ የሀገሪቱ ህግ ሲከለክል ጥያቄውን ውድቅ ሊያደርግ ይችላል፡፡

አንቀፅ 16
የአፈፃፀም ውጤቶችን ስለአለማሳወቅ

የተጠያቂው ወገን ማዕከላዊ ባለስልጣን ማስረጃ መውሰድን አስመለክቶ ለሚቀርበው ጥያቄ የተገኘውን ውጤትና ማስረጃ ለጠያቂው ወገን በጽሁፍ መስጠት አለበት፡፡

አንቀፅ 17
ማስረጃውን የሚሰጡ ሰዎች በአካል ስለመቅረብ

1. በጠያቂው ወገን አቅራቢነት በራሱ ግዛት ውስጥ ማስረጃውን እንዲሰጥ ጠያቂው ወገን የግለሰቡንፈቃደኝነት ሊጠይቀው ይችላል። ጠያቂው ወገንም ስለአበል እና ሌሎች ወጭዎች መጠን እና አይነት ማስረጃ ለሚሰጠው ግለሰብ እንዲያውቀው ያደርጋል። ተጠያቂው ወገንም የግለሰቡን ምላሽ በፍጥነት ለጠያቂው ማሳወቅ አለበት።
2. በአስቸኳይ ጉዳዮች ላይ በአጭር ጊዜ መልስ ለመስጠት ተጠያቂው ወገን ካልተስማማ በስተቀር ማስረጃ የሚሰጠው ግለሰብ በጠያቂው ወገን ግዛት በመሄድ ማስረጃ ለመስጠት የሚደረገው ጥያቄ ጉዳዩን ለመፈጸም ከታቀደበት ቢያንስ ከስልሳ ቀናት በፊት ለተጠያቂው ወገን መተላለፍ አለበት።

አንቀፅ 18
ማስረጃ እንዲሰጡ በእስር ላይ ያሉ ሰዎችን ስለማስተላለፍ

1. በእስር ላይ የሚገኘው ሰው ከፈቀደ እና ተዋዋይ ወገኖች ቀደም ሲል ዝውውርን አስመልክቶ የገቡት የፅሁፍ ስምምነት ካለ ተጠያቂው ወገን ግለሰቡ ማስረጃውን በጊዜያዊነት በሌላኛው ግዛት በመሄድ እንዲሰጥ ሊያደርግ ይችላል።
2. የተላለፈው ግለሰብ በተጠየቀው ወገን ህግ መሰረት በእስር እንዲቆይ የሚገደድ ሲሆን ሌላኛው ወገን ግለሰቡን በእስር ማቆየት አለበት።
3. ጠያቂው ወገን በእስር ላይ የሚገኘውን ግለሰብ ማስረጃውን እንደሰጠ ወዲያውኑ ለጠየቀው ወገን ያስተላልፈዋል።
4. ለዚህ አንቀፅ አላማ ሲባል የተዘዋወረው ሰው በጠየቀው ወገን ለተፈረደበት ዓመት በጠያቂው ወገን እስር ቤት የቆየባቸው ቀናቶች ታሳቢ ይሆናሉ።

አንቀፅ 19
የምስክሮችና የባለሙያዎች የህግ ከለላ

1. በጠያቂው ወገን ግዛት የሚቀርብ ምስክር ወይም ባለሙያ ወደ ግዛቱ ከመግባቱ በፊት ለተፈፀመ፡ ማንኛውም ድርጊቶች ወይም ያለማድረግ ጋር ተያይዞ ሊከሰስ፣ ሊያዝ፣ ሊቀጣ ወይም ደግሞ በማንኛውም ሁኔታ የግል ነጻነቱ ሊገደብ አይችልም። እንዲሁም በእርሱ እና በተጠየቀው ወገን ፍቃድ ካልሆነ በስተቀር ጥያቄው ከቀረበበት ጉዳይ ውጭ ባለ ክርክር ላይ ማስረጃ እንዲሰጥ አይገደድም።
2. የእርሱ በሀገር ውስጥ መኖር አላስፈላጊ መሆኑ ከተገለፀበት አስራ አምስት ቀን በኋላ ወይም ደግሞ ከሀገር ከወጣ በኋላ በፈቃደኝነት ከተመለስ በንኡስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰው መብት

ተግባራዊ መሆን ያቆማል። ነገር ግን ከላይ የተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ግለሰቡ ከአራሱ ቁጥጥር ውጭ በሆነ ምክንያት ከሀገር ያልወጣበትን ጊዜዎች አያጠቃልልም።

3. በአንቀጽ 17 እና 18 መሰረት ማስረጃውን የመስጠት ጥያቄ ያልተቀበለው ግለሰብ በዚሁ ምክንያት ብቻ ለማንኛውም አይነት ገደብ ወይም ሌላ ነፃነቱን ለሚገድብ እርምጃዎች ሊዳረግ አይገባም።

አንቀፅ 20
ማስረጃን ለመውሰድ ስለሚያስፈልጉ ወጪዎች

1. ተጠያቂው ወገን ማስረጃዎችን ለመውሰድ የሚያስፈልጉ ወጪዎችን ይሸፍናል። ነገር ግን ጠያቂው ወገን፦
   ሀ. በአንቀፅ 14(2) በተቀመጠው አግባብ በተለየ ሁኔታ እንዲፈፀም ለማድረግ የሚወጡ ወጪዎችን፣
   ለ. በአንቀጽ 14(5) መሠረት ግለሰቡን ከተጠያቂው ሀገር ለማስወጣት፣ ለማጓጓዝ እና ለማቆያ የሚያስፈልጉ ወጪዎችን፣
   ሐ. በአንቀጽ 17 እና 18 መሠረት ግለሰቡን ወደ ተጠያቂው ሀገር ለመላክ፣ ለማቆየት እና ለመመለስ የሚያስፈልጉ ወጪዎችን እና የአበል ክፍያዎችን መሸፈን አለበት።እነዚሁም ወጪዎች በሚወጡበት ቦታ ባለው ደረጃ እና ደንብ መሰረት ተከፋይ ይሆናል።
   መ. የባለሙያዎች ወጪ እና ክፍያ፣ እንዲሁም
   ሠ. የፍቺ እና የትርጉም ክፍያዎችን ይሆናል።
2. ጥያቂውን ግልፅ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ያልተለመዱ ወጪዎችን ሁለቱ ወገኖች በማን ወገን እንደሚሸፈኑ በመነጋገር ይወስናሉ።

ምዕራፍ አራት
የፍ/ቤት ውሣኔዎችን እውቅና ስለመስጠት እና ስለመፈፀም
አንቀጽ 21
የፍርድ ቤት ውሣኔዎች ተፈፃሚነት ወሰን

1. ይህ ስምምነት ተፈፃሚ ከሆነ በኋላ የሚከተሉት በፍ/ቤት የሚሰጡ ውሣኔዎች በዚህ ስምምነት ውስጥ በተቀመጡት ዝርዝር ሁኔታዎች መሰረት በሌላኛው ወገን ግዛት ውስጥ እውቅና ማግኘት እና መፈፀም አለባቸው።

   ሀ. የፍትሐብሔር እና የንግድ ጉዳዮችን በተመለከተ በፍ/ቤት የሚሰጡ ውሣኔዎች፣
   ለ. በወንጀል ክርክር ጉዳዮች ላይ የጉዳት ካሳ ክፍያዎች እና ለተበዳይ ንብረትን መመለስ አስመልክቶ የሚሰጡ የፍትሐብሔር ውሣኔዎች

2. በንዑስ አንቀፅ 1 የተቀመጠው የፍርድ ቤት ውሣኔ በፍትሐብሔር እና ንግድ ጉዳዮች ላይ በፍ/ቤት የሚሰጥ የስምምነት ሠነዶችን ያጠቃልላል።

አንቀጽ 22
ማመልከቻ አቀራረብ

በፍ/ቤት የሚሰጥ ውሣኔን እውቅና እንዲሰጥ እና እንዲፈፀም የሚቀርብ ማመልከቻ በቀጥታ ጉዳዩን በሚመለከት ተከራካሪ በኩል በሚጠየቀው ወገን ውስጥ ባለ ለጉዳዩ አግባብነት ባለው ፍ/ቤት ይቀርባል። ካልሆነም ውሣኔውን የሰጠው ፍ/ቤት በተጠያቂው ወገን ማዕከላዊ ባለሥልጣን በኩል ለጉዳዩ አግባብነት ላለው ፍ/ቤት እንዲደርስ ይደረጋል፡

አንቀጽ 23
ሊቀርቡ ስለሚቀርቡ ሠነዶች

1. የተሰጡ የፍ/ቤት ውሣኔዎች እውቅና እንዲያገኙ እና እንዲፈፀሙ ለማድረግ የሚቀርብ ማመልከቻ፡-
   ሀ. የተረጋገጠ የውሣኔ ግልባጭ
   ለ. በተሰጠው ውሣኔ ስር ካልተካተተ በስተቀር ውሣኔው የመጨረሻ መሆን እና ተግባራዊ ሊሆን ሊፈፀም እንደሚችል የሚያሳይ ሠነድ፣
   ሐ. ውሣኔው ለተከሣሹ ወገን በተገቢው መንገድ የደረሰው መሆኑን እና የህግ ችሎታ የሌለው ወገን ከነበረ በተገቢው መንገድ የተወከለ መሆኑን የሚያሳይ ሠነድ፣
   መ. ተከራካሪ ወገን በሌለበት የተሰጠ ውሣኔ ከሆነ መጥሪያው ላልቀረበው ተከራካሪ በአግባቡ መውጣቱን የሚያሳይ ሠነድ መቅረብ ይኖርበታል።
2. ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ውሣኔ፣ ሠነዶች እና ማመልከቻው በተጠያቂው ወገን ቋንቋ ተረጋግጦ በሚቀርብ ትርጉም መደገፍ አለበት።

አንቀጽ 24
እውቅና እንዳይሰጥ ወይም እንዳይፈፀም መቃወም

በዚህ ስምምነት አንቀጽ 21 ንኡስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰትን የፍ/ቤት ውሣኔዎችን እውቅና መስጠት እና አፈፃፀም አስመልክቶ በአንቀፅ 6 መሠረት ተቃውሞ ሊቀርብበት የሚችለው፡-

ሀ. ውሣኔው የመጨረሻ ካልሆነ ወይም ውሣኔው በተሰጠበት ወገን ህግ መሠረት ሊፈፀም የማይችል ከሆነ፣

ለ. በዚህ ስምምነት አንቀፅ 25 መሠረት ውሣኔውን የሰጠው ፍ/ቤት ሥልጣን ከሌለው፣ ሐ.ተሸናፊው ወገን የፍ/ቤት መጥሪያው በአግባቡ ካልደረሰው ወይም የህግ ችሎታ የሌለው ወገን በአግባቡ ካልተወከለ፣

መ. ተመሳሳይ የሆኑ ተከራካሪዎች በአንድ አይነት ጉዳይ ላይ በተጠየቀው ወገን ባለ ፍ/ቤት ውስጥ በሂደት ላይ ክርክር ካላቸው፣

ሠ. ውሣኔው በተጠየቀው ወገን ውስጥ ባለ ፍ/ቤት ከተሰጠ ሌላ ውሣኔ ጋር ወይም ተጠያቂው አገር እውቅና ከሰጠው የሶስተኛ ወገን አገር ፍ/ቤት ጋር የማይጣጣም ከሆነ ነው።

አንቀጽ 25
ስለ ፍ/ቤት ስልጣን

1. በዚህ ስምምነት መሠረት ውሣኔ የተሰጠበት ወገን ውስጥ ያለ ፍ/ቤት ሥልጣን እንዳለው ሊቆጠር የሚችለው፡-

ሀ. ክሱ በተመሰረተበት ወቅት ተከሳሹ በግዛቱ ውስጥ ቋሚ የሆነ መኖሪያ ወይም መቆያ የነበረው ከሆነ፣

ለ. ክሱ በግዛቱ ውስጥ በሚገኝ የተከሳሽ ቅርንጫፍ ሥራን መነሻ ያደገ ሲሆን፣

ሐ. ተከሣሹ የሌላውን ወገን ፍ/ቤት ሥልጣን በግልጽ ከተቀበለ፣

መ. ተከሣሹ የፍ/ቤቱ ሥልጣንን ሳይቃወም በዋና ፍሬ ነገር ውስጥ ገብቶ ከተከራከረ፣

ሠ. ውልን በሚመለከቱ አለመግባባቶች በተመለከተ ውሉ በእዚያው ወገን ግዛት ውስጥ ከተደረገ፤ ጉዳዩ በዚያው ወገን የሚገኝ ከሆነ ወይም ውሉ በዚያው ግዛት የተፈፀመ ወይም ሊፈፀም የሚችል ከሆነ፣

ረ. ከውል ውጭ ለሆነ ግንኙነት ጥሰቱ ወይም የዚሁ ውጤት በዚያው ወገን ግዛት ውስጥ ከተከሰተ፣

ሰ. ቀለብ የመስጠት ግዴታን በተመለከተ ክርክሩ በተነሳበት ወቅት ባለመብቱ ቋሚ መኖሪያው ወይም መቆያው በዚያው ወገን ግዛት ውስጥ ከሆነ፣

ሸ. የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ ንብረቱ በሚገኝበት ወገን ግዛት ውስጥ ከሆነ፣

ቀ. ውርስን በተመለከተ የሟቹ ቋሚ መኖሪያ ወይም መቆያው ካለዚያም ዋና የሀብቱ ድርሻ በዚያው የነበረ ከሆነ፣

በ. ግላዊ ጉዳዩን የሚመለከቱ ነገሮችን በተመለከተ ተከራካሪው ቋሚ መኖሪያው ወይም መቆያው በዚያው ወገን ግዛት ከሆነ ነው።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ በሁለቱ ወገን ህግ የተቀመጠውን ብቸኛ የዳኝነት ሥልጣን የጠበቀ ነው። ለዚህም ሲባል ስምምነቱ ወደ ተግባር ሲቀየር በአስቸኳይ ሁለቱም ወገኖች በማዕከላዊ

ባለሥልጣኖቻቸው በኩል በህጐቻቸው ውስጥ ስለሚገኙ ብቸኛ የዳኝነት ሥልጣን በጽሑፍ አንዱ ለሌላው ማሳወቅ ይገባቸዋል።

አንቀጽ 26
እውቅና ስለሚሰጥበት ስርዓት እና አፈፃፀሙ

1. የፍ/ቤት ውሣኔዎች እውቅና የሚያገኙት እና የሚፈፀሙት በተጠያቂው ወገን አገር ውስጥ ባለው የህግ ስርዓት ይሆናል።
2. የተጠያቂው ወገን ፍ/ቤት ወደ ዝርዝር ጉዳዮች ሳይገባ የተሰጡ ውሣኔዎች በዚህ ስምምነት በተቀመጡ ዝርዝር ሁኔታዎች ጋር የተገናዘቡ መሆናቸውን መመርመር አለበት።
3. የፍ/ቤት ውሣኔውን ሙሉ በሙሉ እውቅና ለመስጠት እና ለመፈፀም የማያስችሉ የተለዩ ሁኔታዎች ካሉ የተጠየቀው ወገን በከፊል እውቅና ለመሰጠት እና ለመፈፀም ይችላል።

አንቀጽ 27
እውቅና የመስጠት እና የመፈፀም ውጤት

እውቅና የተሰጣቸው እና እንዲፈፀሙ የተደረጉት የፍ/ቤት ውሣኔዎች በተጠያቂው ወገን ግዛት ውስጥ ባሉ ፍ/ቤቶች እንደተሰጡ ውሣኔዎች ተመሳሳይ ውጤት ይኖራቸዋል።

ምዕራፍ አምስት
የግልግል ውሣኔዎች እውቅና አሰጣጥ እና አፈፃፀም
አንቀጽ 28
እውቅና የሚሰጥበት እና የሚፈፀምበት ሁኔታ

በዚህ ስምምነት የተቀመጡት ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በአንዱ ወገን ግዛት ውስጥ የተሰጠ የግልግል ውሣኔዎች በሌላኛው ወገን ግዛት ውስጥ እውቅና የሚያገኙት እና ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉት፡-

ሀ. የግልግል ውሣኔዎች በተጠያቂው ወገን ህግ መሠረት በልዩ ሁኔታ ወይም ወደ ፊት ሊከሰቱ በሚችሉ ውልን ወይም ከውል ውጭ የሆነ ህግ ነክ የንግድ ግንኙነቶችን መሠረት ያደረገ የተዋዋይ ወገኖች የጽሑፍ ስምምነት ሲኖር እና በውስጡም በዚያው ወገን መታየት እንደሚቻል ሲገልፅ፤

ለ. የግልግል ውሣኔው በተጠያቂው ወገን ህግ መሠረት በግልግል ሊያልቅ የሚችል ጉዳይ ሲሆን ነው።

አንቀጽ 29
የማመልከቻ አቀራረብ

የግልግል ውሣኔዎችን እውቅና እንዲሰጠው እና እንዲፈፀም የሚቀርብ ማመልከቻ በቀጥታ አመልካቹ በተጠያቂው ወገን ውስጥ ባለ ለሚመለከተው ፍ/ቤት ይቀርባል፡፡

አንቀጽ 30
ሊቀርቡ ስለሚገቡ ሠነዶች

የግልግል ውሣኔ እውቅና እንዲሰጠው እና እንዲፈፀም በሚል የሚቀርብ ማመልከቻ፡-

ሀ. ህጋዊ የሆነ የግልግል ውሣኔ ወይም የተረጋገጠ ኮፒው፣

ለ. ህጋዊ የሆነ የግልግል ስምምነቱ ወይም የተረጋገጠ ኮፒው ጋር ተደግፎ መቅረብ አለበት፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሠነዶች በተጠያቂው አገር ቋንቋ ተረጋግጦ በተሰጠ ትርጉም ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

አንቀጽ 31
እውቅናን እና አፈፃፀምን ስለመቃወም

በስምምነቱ አንቀፅ 6 የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ እውቅና እንዲሰጥ እና እንዲፈፀም በሚል የቀረበ የግልግል ውሣኔ ተቃውሞ ሊቀርብበት የሚችለው የተሰጠው ውሣኔ የሚያርፍበት አካል፡-

ሀ. የግልግል ስምምነቱ በተመሰረተበት ህግ መሠት ተደራዳሪ ወገኖች ተፈፃሚ በሚሆንባቸው ህግ መሠረት የተወሰነ ብቁነት ከሌላቸው፤ ስምምነቱ ተዋዋይ ወገኖች በሚመለከታቸው ህግ መሠረት ዋጋ የማይኖረው መሆኑ ወይም ሌላ ጠቋሚ ነገር ከሌለው፣

ለ. ውሣኔው የሚያርፍበት ወገን ስለግልግሉ ወይም የግልግል ሂደቱ በተገቢው መንገድ እንዲያውቀው ካልተደረገ ወይም የራሱን ጉዳይ ማቅረብ ሳይችል ከቀረ፣

ሐ. ውሣኔው ግልግል እንዲደረግበት ተብሎ ከተሰጠው ጉዳይ በላይ ሲሆን፣

መ. የግልግል አድራጊው ባለሥልጣን ወይም የግልግል ሥርዓት ስብጥሩ ተዋዋይ ወገኖች ባስቀመጡት ስምምነት መሠረት ካልሆነ፤ ወይም ስምምነት ካላደረጉም ግልግሉ በተደረገበት ወገን ህግ መሠረት ሳይሆን ሲቀር፣

ሠ. የተሰጠው ውሣኔ በተዋዋዮች ዘንድ አስገዳጅ ካልሆነ፤ ውድቅ ከተደረገ ወይም ስምምነቱ በተደረገበት ወገን በሚገኝ አግባብነት ባለው ባለሥልጣን የስምምነቱ መቋረጥ ሲረጋገጥ

ብቻ ይሆናል።

ምዕራፍ ሰድስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 32
በህጉ መሠረት ማስረጃዎችን ስለመለዋወጥ

ተዋዋይ ወገኖች ይህን ስምምነት ተግባራዊ ከማድረግ ጋር ተያይዞ ተፈፃሚነት ያላቸውን ህጎች እና የዳኝነት ተግባሩን አስመለክ ጥያቄ ሲቀርብ ተዋዋይ ወገኖች መረጃዎችን መለዋወጥ ይኖርባቸዋል።

አንቀጽ 33

በዲፕሎማቲክ ወይም በቆንስላ ተወካይ አማካኝነት የሚደረግ የሰነዶች አገልግሎት ወይም መረጃዎችን ስለመውሰድ

የአንደኛው ወገን ህግን ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ እንዲሁም የሀይል እርምጃ እስካልተወሰደ ድረስ በዲፕሎማቲክ ወይም በቆንስላ ተወካዮች በኩል በሌላኛው ወገን ግዛት ውስጥ ከሚገኙ ዜጎች ማስረጃዎችን መውሰድ እና ሰነዶችን የመገልገል ተግባር ማከናወን ይቻላል።

አንቀጽ 34
የህጋዊነት ጥያቄን ስለማስቀረት

በተዋዋይ ወገን ፍ/ቤቶች ወይም በሌላ አግባብነት ባለው ባለስልጣን ተዘጋጅተው በፀደቁ እና በማዕከላዊ ባለስልጣኖች በኩል የሚተላለፉ ማንኛውም ሰነዶች ለዚህ ስምምነት ሲባል ከማንኛውም አይነት ህጋዊነትን ከሚያስነሱ የፎርም ጥያቄዎች ነጻ ናቸው።

አንቀጽ 35
ከሌሎች ስምምነቶች ጋር ስለሚኖር ግንኙነት

ይህ ስምምነት ተዋዋይ ወገኖች በሌሎች ስምምነቶች እና ማስፈፀሚያዎች ስር የገቧቸውን ግዴታዎች ሊጥስም ሆነ በመሰል ስምምነቶች መነሻነት እየተሰጠ ያለውን እና የሚሰጠውን የጋራ ትብብር ድጋፍ ሊከለክል አይችልም።

አንቀጽ 36
አለመግባባቶች ስለሚፈቱበት ሁኔታ

ይህን ስምምነት ከመተርጎም እና ከመፈፀም ጋር ተያይዞ የሚነሱ አለመግባባቶች በማዕከላዊ ባለስልኖች አማካኝነት ስምምነት ላይ ካልተደረሰ በዲፕሎማሲያዊ መንገዱ በሚደረግ ምክክር መፍትሄ እንዲገኝለት ይደረጋል።

ምዕራፍ 7
የማጠቃለያ ድንጋጌዎች
አንቀጽ 37
ወደ ሥራ ስለመግባት እና ስለማቋረጥ

1. ይህ ስምምነት ለማፀደቅ የተዘጋጀ ነው።ተዋዋይ ወገኖች በዲፕሎማሲያዊ ማስታወሻ ስምምነቱ መፅደቁን አንዱ ለሌላው ከገለፀበት 30 ቀናት በኋላ ተግባር ላይ ይውላል።
2. አንደኛው ወገን በማንኛውም ጊዜ ዲፕሎማሲያዊ መንገዶችን ተጠቅሞ በጽሑፍ ለሌላኛው በማሳወቅ ስምምነቱን ሊያቋርጥ ይችላል። መቋረጡ ተግባር ላይ የሚውለው ሌላኛው ወገን ማስታወቂያው ከደረሰበት 180 ቀናት በኋላ ይሆናል።
3. ስምምነቱን ማቋረጥ የተጠበቀ ቢሆንም ከመቋረጡ በፊት ሌላኛው ወገን የተቀበላቸው ማንኛውም ጥያቄዎች በዚህ ስምምነት መሠረት ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል።

አንቀጽ38
ስለማሻሻል

ተዋዋይ ወገኖች በሚስማሙባቸው ሁኔታዎች መሰረት ስምምነቱ በማንኛውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል። የተደረጉ ማሻሻያዎች የዚህ ስምምነት አካል ይሆናሉ።

እኩል እውቅና ባላቸው በአማርኛ፣ በቻይንኛ እና እንግሊዝኛ ቋንቋ ተተርጉሞ ልዩነት በሚኖር ጊዜ የእንግሊዝኛው ትርጉም የበላይ እንደሚሆን ታውቆ በተዋዋይ ወገኖች በመንግታት በአግባቡ በተወከሉት ከዚህ በታች በተጠቀሱት በ_____ቀን _____ዓ.ም ስምምነቱ ተፈርሟል።

የቻይና ህዝባዊ ሪፐብሊክ መንግሥት	የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት